Government of Western Australia
North Metropolitan Health Service
Mental Health, Public Health and Dental Services

# ፈጣን መመሪያ:
# ለጥርስ ጤና ጥበቃ አገልግሎቶች (DHS)

በወስተርን አውስትራሊያ (WA) እንደ ከፍተኛ የህዝባዊ ጥርስ ጤና ጥበቃ አገልግሎቶች ስለሆነ የገንዘብ እርዳታ በአስተዳደር ክልል መንግሥት በኩል ይቀርባል። DHS መፈተሽ የሚችለው ለመጀመሪያ ጊዜ በ1926 ዓ.ም ለህዝባዊ ጥርስ ጤና ጥበቃ ባለሙያ በህዝ ባዊ ጤና ጥበቃ መምሪያ የተቀጠረበትን ታሪክ ነው።

## የእኛ አገልግሎቶች

የጥርስ ጤና ጥበቃ አገልግሎቶች (DHS) ለወስተርን አውስትራሊያ ህዝብ የጥርስ ጤና ጥበቃ አገልግሎቶችን በሚከተሉት አገልግሎት ምንጮች ያቀርባል።

## በትምህርት ቤት የጥርስ አገልግሎት (SDS)

በትምህርት ቤት ጥርስ አገልግሎት (SDS) ህዝባዊ የጤና ጥበቃ መርሃ ግብር እንደሆነ እና በወስተርን አውስትራሊያ ትምህርት መምሪያ ተቀባይነት ባገኘ ለሚማሩ እድሚያቸው ከ5 እስከ 16 ዓመት ለሆኑ ተማሪዎች ወይም እስከ ክፍል/year 11 እስኪጨርሱ ድረስ አጠቃላይ ለሆነ የጥርስ እንክብካቤ ያለክፍያ በነጻ ይቀርብላቸዋል።

የSDS በሞላው አስተዳደር ክልል በተወሰነ ቦታ እና በሚንቀሳቀስ የጥርስ ህክምና ማእከላት (DTC) ከአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ጋር የተቀናጀ ነው።

ተማሪዎች በመጀመሪያ ዓመት ሲመዘገቡ የመጀመሪያ እንክብካቤ ኮርስ እንደቀረበላቸውና ከዚያም ለወደፊት ላላቸው ክሊኒካል ፍላጎት ምርመራ እንዲያገኙ ስማቸው በመጠባበቂያ ተራ ይቀመጣል። እንደ አስፈላጊነቱ፤ የአስቸኳይ ጥርስ እንክብካቤ አገልግሎት ይቀርባል።

## አጠቃላይ የጥርስ እንክብካቤ አገልግሎት

አጠቃላይ የጥርስ ክሊኒኮች (GDC) የሚሰሩት በወስተርን አውስትራሊያ/WA አገር ውስጥ ባሉት በሞላው ከተማ ክልል ውስጥ ይሆናል። በወስተርን አውስትራሊያ/WA በፋይናንስና በጂኦግራፊ ለሚፈቅወድላቸው ነዋሪዎች ለአጠቃላይና አስቸኳይ ጥርስ እንክብ ካቤ ክፍያ ከመንግሥት የማካካሻ ገንዘብ ያገኛሉ። ለእንክብካቤ በGDC ስለመሄድ ለፈቃድ ማስገኛ አስፈላጊ ነገሮች:

- ወቅታዊ የሆነ የጤና ጥበቃ ካርድ ወይም የጥሮታ ቅናሽ ዋጋ ካርድ ላላቸው ሰዎችና የSDS ለሚፈቀድላቸው፤ እና
- እድሜያቸው ከ0 እስከ 4 ዓመት ለሆኑ ህጻናት በወላጆቻቸው ጤና ጥበቃ ወይም በጥሮታ ቅናሽ ዋጋ ካርድ ላይ ስማቸው ለሚታይ ህጻናት ይሆናል።

ለአስቸኳይ እንክብካቤ እንደ አስፈላጊነቱ በቅድሚያ ይቀርባል። አስቸኳይ የሆነ እንክብካቤ ለሚፈልጉ ወላጆች በሙሉ በአካባቢያ ቸው ላለ ህዝባዊ የጥርስ ክሊኒክ ደውለው ቀጠሮ ማስያዝ እንዳለባቸው ነው። ወላጆች ላላቸው የጥርስ ችግር በአስቸኳይ ምርመራ እንዲደረግ ይፈልጋሉ ታዲያ በጣም ከባድ የሆነ ችግሮች ላለባቸው ታካሚዎች የ DHS ቅድሚያ መስጠት ይችላል። እባክዎ ያለ ቀጠሮ ወደ ክሊኒኮች አይምጡ።

አስቸኳይ ያልሆነ የጥርስ እንክብካቤ ለማያስፈልጋቸው ታካሚዎች በተራ ጥበቃ ምዝገባ ላይ ስማቸውን ማስቀመጡ የሚጠቅመው ካለው መገልገያ አቅርቦት በላይ ለአገልግሎቶች ጥያቄ ስለሚበዛ እና አገልግሎት ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማረጋገጥ ነው። የታካሚዎች ስም ተራ ምዝገባ በሚደርስበት ጊዜ የGDC ይነግራቸዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ እንክብካቤ መጠናቀቅ በመቀጠል፤ ወላጆች ለቀጣዩ በተ ደጋጋሚ ለሚደረግ የምርመራ ማጣሪያ በእንደገና ጥሪ ጥበቃ ምስገባ/Recall Waiting List ላይ ስማቸው ይቀመጣል።

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይቀጥላል

## ለየት ያለ የጥርስ ህክምና አገልግሎቶች

- ከዚህ ለሚከተሉት ለየት ያሉ የታካሚ ቡድኖች በመንግሥት ተመላሽ ክፍያ ድጎማ የጥርስ እንክብካቤ ይቀርብላቸዋል:
- በከተማ ክልል የእድሜ አንጋፋ እንክብካቤ መስጫ መኖሪያ መገልገያዎች ነዋሪዎች በስምምነት በየዓመቱ የጥርስ ማጣሪያ ምርመራ በነጻ ያገኛሉ
- በከተማ ክልል ውስጥ ላሉ እስረኞች እና በዋና የገጠር ጠባይ ማረሚያ አገልግሎት መገልገያዎች መምሪያ (በአጠቃላይ እስር ቤት- ባሉ ክሊኒኮች)
- ከመማር ጉዳተኛ ወይም ለየት ያለ በአእምሮ ላይ ከሚፈጠር ጉዳት ጋር በተዛመደ የእድገት ጉድለት ላለባቸው ለሚፈቀድላቸው ግለሰቦች
- ፈቃድ ካለው የስነፕ-አእምሮ ሆስተል እና ሆስፒታሎች ለተላኩ በግራይላንድስ/Graylands ሆስፒታል ውስጥ ላሉ ታካሚዎችና ተመላላሽ ታካሚዎች
- በከተማ ክልል በአምቡላንስ ላልመጡ ታካሚዎች ከህክምና መላኪያ ጋር
- የጎበጠ ስፓይናል ጉዳት ላለባቸው በተሽከርካሪ ወንበር/ዊልቸው ለሚጠቀሙ ግለሰቦች

## ለጥርስ ህክምና ክፍያ ዋጋ ድጎማ አሰራር

እንዲሁም የግገንዘባዊ ወይም በጂዮግራፊ አቀማመጥ ማግኘት ለሚፈቀድላቸው ሰዎች DHS ለአጠቃላይና አስቸኳይ የጥርስ እንክብ ካቤ ህክምና ድጎማ ክፍያ እንዲያገኙ የሚቀርበው:

- በገጠር ታካሚዎች የጥርስ ዋጋ ክፍያ ድጎማ አሰራር በኩል እንደሆነ: በገጠር ህዝባዊ የጥርስ ጅክምና ክሊኒኮች በኩል የሚመሰገን የጥርስ እንክብካቤ እንደሚቀርብ እና ለመንግሥት የጥርስ ክሊኒክ ለመጠቀም ያለምንም እንቅፋት በአካባቢ ባሉት ቦታዎች ይካሄዳል። የጥርስ እንክብካቤ የሚቀርበው በ DHS ተቅወባይነት ባላቸው የግል ጥርስ ባለሙያዎች ይሆናል።
- በከተማ ክልል ታካሚዎች የጥርስ ዋጋ ክፍያ ድጎማ አሰራር በኩል እንደሆነ: የገንዘብ እርዳታ ሲፈቀድ፤ በህዝባዊ የጥርስ ቆጠሮ ጥበቃ ዝርዝር ለሚፈቅወድላቸው የከተማ ክልል ታካሚዎች ምናልባት አስቸኳይ ላልሆነ አጠቃላይ ጥርስ እንክብካቤ ለማካሄድ የዋጋ ክፍያ ድጎማ ፈቃድ ተሳታፊ ለሆነ የግል ጥርስ ባለሙያዎች ሊሰጥ ይችል ይሆናል።
- ለግላዊ የጥርስ አጥንት/Orthodontic ባለሙያ የዋጋ ክፍያ ድጎማ አሰራር – በገጠር ለሚፈቅወድላቸው ታካሚዎች ማግኘት የሚችሉት ለቤት ቅርብ በሆነ ለጥርስ አጥንት/Orthodontic ባለሙያ አገልግሎቶች የሚሆን የዋጋ ክፍያ መደጎሚያ ለማግኘት ለDHS በማነጋገር ይሆናል፤ ይህም በአሁን ጊዜ ለልዩ ባለሙያ አገልግሎቶች የዋጋ ክፍያ ድጎማ የሚቀበው በፐርዝ ውስጥ ብቻ ስለሆነ ነው።

## ለጎልማሶች ዋጋ መጠንና ክፍያዎች

ሁሉም የጥርስ ዋጋ ክፍያዎች በኮመንወልዝ ያገለገለ ሽማግሌ ጉዳይ መምሪያ አሰራር የጥርስ ክፍያ መሰረት ይሆናል።፡

በህዝባዊ የጥርስ ክሊኒክ ወይም ተሳታፊ በሆነ የግል ጥርስ ክሊኒክ በኩል ለሚቀርብ ህክምና የተካሄድ ወጪ ባላቸው የሰንተርሊንክ ገቢ መጠን መሰረት በማድረግ በወስተርን አውስትራሊያ መንግሥት ቢበዛ እስከ 75% የዋጋ ክፍያ ድጎማ ይቀርባል። የቀረው የዋጋ ክፍያ ክፍል የታካሚው ሃላፊነት ስለሆነ የመክፈያ አካውንት ይሰጣል። ያልተከፈል አካውንት ላለባቸው ታካሚዎች አስቸኳይ ላልሆነ እንክብካቤ ቀጠሮ ማስያዝ አይችሉም።

## በጣም የራቀ ገጠር አካባቢዎች ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች

በጣም እሩቅ ገጠር አካባቢዎች ላሉት የDHS ብቸኛ የሆነ የጥርስ ህክምና አቅራቢ እንደሆነ፤ ሁሉም ታካሚዎች ለጥርስ እንክብካቤ በህዝባዊ የጥርስ እንክብካቤ መስጫ ክሊኒክ መጠቀም ይችላሉ። ለእንክብካቤ ዋጋ ክፍያ ድጎማ ለማይፈቀድላቸው ታካሚዎች ሙሉን ዋጋ መክፈል ይኖርባቸዋል።

## ለበለጠ መረጃ እባክዎን ከእርስዎ ጥርስ ባለሙያ ጋር መነጋገር

### የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ውቀውይም አስተያየት መስጠት ከፈለጉ?

ይህ ሰነድ በሌላ አማራጭ የተለያየ ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል፤ ይህም በጥያቄ በ braille, audio tape ወይም electronically ይሆናል.

Communications Officer, Dental Health Services
Locked Bag 15, Bentley Delivery Centre, WA 6983

(08) 9313 0555

publications@dental.health.wa.gov.au

www.dental.wa.gov.au

በዚህ ሰነድ የተጠቀሙት ማንኛውም ቅርጽ/ስእል ለመግለጫ ተብሎ ብቻ እንደሆነ ይህም ለአጠቃላይ መመሪያ ለማቅረብ ብቻ ነው።

CONSUMER REVIEWED

HealthyWA Health information for Western Australians

© 2020 Dental Health Services WA. All rights reserved.